# የመንጎኮካል በሽታ – ተጨባጭ ነገሮች

## (Meningococcal disease – the facts)

Amharic

### የመንጎኮካል በሽታ ምን’ድ ነው?

ይህ በሽታ በጣም ያልተለመደ ሲሆን ነገር ግን ወደ መኒንጃይቲስ ወይም ደም መመረዝ በሚቀየርበት ጊዜና ማበጥ ሲጀምር በጣም ኃይለኛ ሕመም ይኖረዋል። ‘መኒንጃይቲስ’/Meningitis ማለት የአንጎልና የስፓይናል ኮርድ/አከርካሪ መሸፈኛ መከላከያ ሲያብጥ ማለት ነው። ‘ሰፕቲካሚያ’/Septicaemia ማለት ደም ሲመረዝና በበለጠ በሰውነት አካል በመሰራጨት ቁስለት/በሽታ ሲያስከትል ማለት ይሆናል።

የመንጎኮካል በሽታ ‘meningococci’ ተብሎ በሚጠራ የባክቴሪያ ህዋሳት አማካኝነት ይመጣል። ብዙ የተለያዩ የmeningococci ባክቴሪያ ቡድኖች አሉ። በቪክቶሪያ ውስጥ ለብዙ በሽታዎች ምክንያቶች ሁለት ቡድኖች ሲሆኑ እነዚህም Serogroup B እና Serogroup C ይባላሉ።

### የመንጎኮካል በሽታ ምን ያህል አደገኛ ነው?

የመንጎኮከስ በሽታ ያልተለመደ ችግር ቢሆንም ይህ በጣም አደገኛ በሽታ ነው። በሽታው ቶሎ ብሎ ሊተላለፍ ሲችል ከተያዙት 10% የሚሆነው ለሞት ሊያጋልጥ ይችላል። የሽታው ምልክት ቶሎ ብሎ ከታወቀ ትክክለኛ መድሃኒት ፀረ-ህዋሳት ወዲያውኑ በመስጠት ብዙዎቹ በሽተኞች ሙሉ በሙሉ እንደሚድኑ ነው።

ከበሽታው ያገገሙ አንድ አራተኛ የሆኑት ሰዎች ከዳኑ በኋላም ችግር ይጋጥማቸዋል። ከተለመዱት አንዳንድ ችግሮች ውስጥ የራስ ምታት፣ በአንድ ወይም በሁለቱም ጆሮ አለመስማት፣ የጆሮ ህመም [በጆሮ ላይ የድወል ስሜት]፣ መደብዘዝና ሁለት ሁኖ መታየት፣ በመገናኛ ላይ ሕመምና ድርቀት፣ ለመማር ችግሮችን ያካተተ ይሆናል። እነዚህ ችግሮች ከጊዜ ጋር እንደሚሻሻሉ ነው

### የመንጎኮካል በሽታ ከየት ይመጣል?

meningococci ባክቴሪያዎች የተለመዱ እና ከአስር ሰዎች አንዱ የባክቴሪያው ‘ተሸካሚ’ ሲሆን ከጉሮሮ በስተኃላ ወይም በአፍንጫ ላይ ይገኛል። አብዛኛው የባክቴሪያ ተሸካሚ በወጣት አዋቂ ሰው ላይ ሲሆን በህፃናትና በእድሜ በገፉ ሰዎች ላይ ችግሩ ብዙም አይታይ። የmeningococci ባክቴሪያ በሰዎች ላይ ብቻ ሲገኝ በእንስሳትና አጠቃላይ በአካባቢ ላይ አይታይም።

### የመንጎኮካል ‘ተሸካሚ’ ምን’ድ ነው?

በአጠቃላይ አዋቂዎችና ህፃናት ላይ የበሽታ ችግር ሳይከሰት የባክቴሪያ ጀርሙን ሊሸከሙ ይችላሉ። የምርምር ውጤት እንደሚያሳየው ተሸካሚ በመሆን ሰዎችን ከአደገኛ የmeningococci ባክቴሪያ ሊከላከልላቸው እንደሚችል ነው። ሰዎች ሳይታወቃቸው የባክቴሪያ ተሸካሚ ሲሆኑ ከጥቂት ሳምንታት ወይም ወራት በኃላ ያለ ምንም ሕክምና በተፈጥሮ በራሱ እንደሚጠፋ ነው።

### የመንጎኮካል በሽታ ማን ነው ያለበት?

በማንኛውም እድሜ ገደብ ላለ ሰው በሽታው ሊከሰት ይችላል ነገር ግን እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ላሉ ህፃናት ለችግሩ በጣም ይጋለጣሉ። እንዲሁም እድሚያቸው ከ15 እስከ 24 ዓመት ያሉ ወጣቶችና አዋቂ ሰዎች ለችግሩ በጣም ይጋለጣሉ ነው።

በዚህ በሽታ የተያዙ ሰዎች ሕመሙ በአማካኝ እስከ 3-4 ቀናት ይቆያል ነገር ግን እስከ 7 ቀናትም ሊቆይ እንደሚችል ነው። አንዳንድ ጊዜ መጠነኛ ወረርሽኝ ሲፈጠር ከአንድ ሰው በላይ ሊታመም ይችላል ይሁን እንጂ የእያንዳንዱ በሽታ መንስኤ አይመሳሰልም።

በዚህ በሽታ የሚለከፉ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ከሲጋራ አጫሾች ጋር የቅርበት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ላይ እንደሚሆን ነው። እንዲሁም በቫይረስ መታመም [በተለይ የኢንፍሎንዛ በሽታ] በጣም የተለመደ ነው። በሽታውን ለመከላከል ከሲጋራ ማጨስና ከአቧራ አካባቢ መራቁ ይረዳል።

### የበሽታው ምልክቶች ምን’ድ ናቸው?

የመኒጎኮካል በሽታ ያለበት ሰው በጣም ይታመማል፣ ቀደም ሲል ከነበራቸው ስሜት ጋር ሲወዳደር የሕመም ስሜት ያድርባቸዋል። በሽታውን ለመለየት ብዙ ምልክቶች እንዳሉት ቢሆንም በተለይ ጥቂቶቹ በጣም አስፈላጊ ይሆናሉ። የዚህ ዓይነት በሽታዎች በአብዛኛው እነዚህን ምልክቶች ብቻ ሲኖራቸው ሁሉም ባንድ ጊዜ እንደማይፈጠሩ ነው።

የመኒጎኮካል በሽታ ምልክቶች የሚያካትተው:

**በህፃናትና በታዳጊ ህፃናት ላይ:**

- ትኩሳት
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- ብስጩ መሆን
- ከመጠን ያለፈ ድካም ወይም መዝለፍለፍ
- ለሚደረገው እንክብካቤ መጥላት
- ማስታወክና/ወይም ተቅማጥ
- ከብርሃን ላይ መሰወር
- ማንጎላጀት
- የአእምሮ መታወክ ወይም መንቀጥቀጥ
- ቀይ ያበጠ የነጠብጣብ ሽፍታ ወይም ትልቅ ጠባሳ

**በትላልቅ ህፃናትና በአዋቂ ሰው ላይ:**

- የራስ ምታት
- የብርሃን ጥላቻ (ብርሃን ያለበትን መጥላት)
- ትኩሰሳት
- ማስታወክና/ወይም ተቅማጥ
- የአንገት መታወክ ወይም ሕመም
- የወገብ ሕመም

- በመገናኛ ላይ ሕመም ወይም የጅማት መታወክ
- በአጠቃላይ የሕመም ስሜት፣ ምግብ ማቆም
- ማንገላጀት፣ መደናገር
- ቀይ ያበጠ የነጠብጣብ ሽፍታ ወይም ትልቅ ጠባሳ

በታዳጊ ህፃናት ላይ ምልክቶቹ ላይታይ ይችላል ይህም ትኩሳት፣ የፊት መገርጣት፣ የማስታወክ፣ ሕይወት መሳት [መዘረረር፣ መደንዘዝ፣ መራመድ አለመቻል፣ ወይም መመገብ አለመቻል] እንዲሁም የቆዳ ሽፍታ ዋናው የበሽታ ምልክት ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ የበሽታ ምልክቶቹ በተሎ መታየት ሲችሉ መ፟ኒንጎኮካል በሽታ የያዛቸው ሰዎች ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሕመሙ ሊብሰባቸው ይችላል።

በመ፟ኒንጎኮካል የደም መመረዝ ሲበከሉ ሁልጊዜ የቆዳ ሽፍታ ምልክት እንደሚታይ ነው። የቆዳ ሽፍታው በማንኛውም የሰውነት አካል ላይ ሊታይ ይችላል።

ቤተሰብዎትንና ጥሩ ጓደኖችዎን ከሌላው ሰው በበለጠ እንደሚያውቋቸው ነው። ከርስዎ ጋር የሚቀርብ ሰው እነዚህን ምልክቶች ካለበትና ከበፊቱ በበለጠ የሚታመም ከሆነ ወዲያውኑ የሕክምና እርዳታ እንደሚያስፈልግ ነው። ወጣቶች ከታመሙ ለብቻቸው መተው ተገቢ አይደለም። ቀደም ብሎ ችግሩን በማወቅ ሕክምና ማድረጉ ጠቃሚ ይሆናል።

#### የመንገኮካል በሽታ እንዴት ይሰራጫል?

በሽታውን ለማሰራጨት አስቸካሪ ይሆናል። የበሽታ መንስኤ ጀርሙ ከሰውነት ውጭ ከተወሰነ ሰከንድ መኖር አይችልም። ስለዚህ በውኃ አቅርቦት፣ በመዋኛ ገንዳዎች፣ በህንፃዎች ወይም በፋብሪካ በኩል እንደማይተላለፍ ነው።

ባክቴሪያው ሊተላለፍ የሚችለው አብሮ ብዙ ጊዜ በመኖርና የቅርበት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ብቻ ይሆናል። በምትኖርበት መጠለያ እንደ የተማሪዎች መኖሪያ አዳራሽና የወታደር ካምፖች ላይ በሽታው በበለጠ ችግር ሊያመጣ ይችላል።

#### የመንገኮካል በሽታን እንዴት ማከም ይቻላል ወይ?

ምናልባት በመንገኮከስ የማንጃይተስ [አንገት እብጠት] ወይም የደም መመረዝ ጥርጣሬ ካለ ወዲያውኑ የፀረ-ህዋሳት/አንቲባዮቲክ መድኃኒት በመርፌ መልክ በመስጠት በሽተኛው ሆስፒታል እንዲገተኛ ይደረጋል።

#### የመንገኮካል በሽታን እንዴት መከላከል ይቻላል ወይ?

Serogroup B የተባለውን የበሽታ ቡድን ለመከላከል ከትባት መርፌ የለውም። ሁለት ዓይነት ከትባቶች ለ Serogroup C ያካትታል:

1. Conjugate meningococcal C: ይህ ከትባት በማንኛውም እድሜ ላለ ቡድን ማለት ህፃናትን ያካተተ ለስድስት ሳምንታት ይሰጣል። እነዚህ ከትባቶች Serogroup C የተባለውን በሽታ በሚገባ ለመከላከል እና የረጅም ጊዜ የበሽታ መከላከል አቅም እንዲኖር ይረዳሉ
2. Polysaccharide meningococcal: ይህ ክትባት በአውስትራሊያ ውስጥ ያልታዩ ብዙ የበሽታ ቡድኖችን ያካተተ ቢሆንም ወደ አፍሪካና ኤሲያ እንዲሁም ከፒልግሪም ወደ ሃጅ ለሚጓዙ ሰዎች ጠቃሚ ይሆናል። ነገር ግን እድሚያቸው ከሁለት ዓመት ላሉ ህፃናት ይህ ክትባት አይሰጥም። ይህ ክትባት እስከ ሶስት ዓመት ብቻ ከበሽታው እንደሚከላከል ነው።

#### ሁኔታው ሲከሰት ምን ይደረጋል?

ሁኔታውን በቅርበት ሆኖ በመከታተል በበለጠ ቁስለት/በሽታ ከማስከተሉ በፊት ለመከለላከያ የሚሆን የፀረ-ህዋሳት/አነንቲባዮቲክ መስጠት ይቻላል። እነዚህ የሚከታተሉ ሰዎች በአንድ ቤት ያሉ አባላት፣ የሴት/የወንድ ጓደኛ እና ችግሩ ከመከሰቱ በፊት ለሰባት ሌሊት አብሮ ያድር የነበረ ማንኛውም ሰው ሊሆን ይችላል። ሌሎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች እንደ ጓደኞች እና የሥራ ባልደረቦች ሕክምና እንደማያስፈልጋቸው ነው። ሁኔታው በሚከሰትበት ጊዜ የሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ ምን መደረግ እንዳለበት ምክር በመስተተና እንዲሁም በቅርበት ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ትክክለኛ ሕክምና በማድረግ በሽታው እንዳይስፋፋ መደረጉን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

በጣም ቅርበት ያላቸው ሰዎች ብቻ ሕክምና እንደሚያስፈልጋቸው ነው። ይህም በሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ በኩል አስፈላጊው ቅንጅት ይደረጋል። የፀረ-ህዋሳት/አንቲባዮቲክ ለማያስፈልጋቸው ሰዎች መድኃኒቱን በመስጠት ችግሮች ሊፈጥር ይችላል።

በሽተኛው አንዴ ከዳነ በኋላ ቁስል ሊፈጥርበት አይችልም እንዲሁም ወደ መዋእለ ህፃናት፣ ት/ቤት ወይም ወደ ሥራ ያለችግር መመለስ ይችላሉ። በቤታቸው ግንኙነት ያላቸውና የፀረ-ህዋሳት/አነንቲባዮቲክ መድኃኒት ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ት/ቤት ወይም መዋእለ ህፃናት ተመልሰው መጀመር ይችላሉ።

#### ልጄ መኒንገኮካል በሽታ ከያዘው ሰው ጋር ግንኙነት ካለው ምን ማድረግ እችላለሁ?

በሽታው በት/ቤት ወይም በሥራ ቦታ በኩል እንደማይተላለፍ ነው። በልጅዎት ላይ የሚከሰተውን ማንኛውም ምልክት በጥንቃቄ መከታተልና የሚጠራጠሩ ከሆነ በቀጥታ ሕክም ለማግኘት መጣር ይሆናል።

#### ስለ መኒንገኮካል በሽታ በበለጠ ማብራሪያ ማግኘት

ስለ መኒንገኮካል በሽታ በበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት:

የሕዝብ ጤና/Public Health
የሰብዓዊ አገልግሎት መምሪያ/Department of Human Services
ፖ.ሳ.ቁጥር/GPO Box 4057
Melbourne 3001

ስልክ ቁጥር: 9637 4000

#### ለበለጠ ማብራሪያ ከዚሕ በሚከተለው ዌብሳይት ላይ ቀርቧል

Meningitis Foundation of America:
http://www.musa.org

Meningitis Trust:
http://www.meningitis-trust.org.uk

The Meningitis Research Foundation:
http://www.meningitis.org.uk